| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ርእስ ፡ አንቀጽ ። |
| ርእስ ፤ | *"ኢትዮጵያዊ ፡ ሀገራዊነት ፡ ይለምልም !"* |
| ደራሲ ፤ | *"ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ።* |
| ዕለት ፤ | መስከረም ፡ 2018 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | *"ሥልጡንሕዝብና"* ፥ ቍ.2018-001 |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ርእስ ፡ አንቀጽ ።

editorial | éditorial | اِفْتِتَاحي

# ኢትዮጵያዊ ፡ ሀገራዊነት ፡ ይለምልም !

**የ፶ ፡ ዓመቱን ፡ የጥፋት ፡ ድግስ ፥ ዐምሐራ ፡ በኢትዮጵያዊነት ፡ ዳግም ፡ አሸራሸቶታል!**

———




የጭፍጨፋው ፡ ዘመን ፡ ፳፻፲፯ ፡ ዓ.ም. ፡ ተጠናቅቆ ፡ በዐዲስ ፡ የጭፍጨፋ ፡ ዘመን ፡ ፳፻፲፰ ፡ ዓ.ም. ፡ ሊተካብን ፡ ይመስላል ። እንዳይተካብንማ ፥ በ፳፻፲፯ ፡ ዓ.ም. ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ትግሉን ፡ አስተባብሮ ፡ ኢ..ፌ.ዴ.ሪ. ፡ የተባለውን ፡ የውንብድና ፡ አገዛዝ ፡ ለማስወገድ ፡ ሲችል ፥ ሳይፈጽመው ፡ ቀርቷል ።

ለምን ፡ ይኾን ፡ ምልክዮሽ [1] ፡ ይህን ፡ ያኽል ፡ ቂም ፡ እና ፡ በቀል ፣ ጥላቻ ፡ እና ፡ ፍራቻ ፣ ትፀርርት ፡ እና ፡ ጥቃት ፡ በኢትዮጵያ ፡ እና ፡ በሀገራዊ ፡ ሕዝቧ ፡ በዐምሐራ ፡ ላይ ፡ ያሳየው ፡ እና ፡ የሚያሳየው ∴ ዐምሐራ ፡ መቼ ፡ ነው ፡ ባሕርን ፡ ተሻግሮ ፡ ማንን ፡ ያጠቃው ∴ ወይስ ፥ ገና ፡ ለገና ፥ *"ለዓለማዊ ፡ ልዕልናዬ ፡ ዕንቅፋት ፡ ይኾንብኛል"* ፡ ብሎ ፡ ምልክዮሽ ፡ ዐማራን ፡ በጠላትነት ፡ አይቶ ፡ ይኾን ∴ ይህ ፡ ቢኾን ፡ ምክንያቱ ፥ ድርጊቱ ፡ ፀረ-ሥልጣኔነትን ፡ ያመለክታል ።

በኹለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ዋዜማም ፡ ይኸው ፡ የምልክዮሽ ፡ መጨነቅ ፡ የወልወልን ፡ ተንኰል ፡ ፀንሶ ፥ ኹለተኛውን ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ወልዶ ፡ አይቀጡ ፡ ቅጣትን ፡ ተቀጥቶ ፡ ነበር ።

ልመናን ፡ መለመን ፡ ልመና ፡ ኀይል ፡ መኾኑን ፡ ለሚያውቅ ፡ ብቻ ፡ ነውና ፥ በተለይ ፡ ደግሞ ፡ ውንብድና ፡ እንጂ ፡ ሕጋዊ ፡ መንግሥት ፡ በሌለበት ፡ በዛሬው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኹኔታ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊ ፡ ሕዝብ ፡ ዐምሐራ ፡ በሕግ-አምላክ ፡ ማለቱን ፡ አቁሟል ። ለእግዚእናው ፡ መከበር ፡ መሥዋዕትነትን ፡ ከመክፈል ፡ እና ፡ ዐዲስ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥትን ፡ ከመመሥረት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ መፍትሔ ፡ እንደሌለ ፡ ተረድቶ ፥ ነፍጥ ፡ አንሥቶ ፡ ዕለት ፡ በዕለት ፡ የዐርበኝነት ፡ ትግሉን ፡ እያጋመው ፡ ወደመጨረሻው ፡ ድል ፡ ይገሠግሣል ።

ግሥጋሤው ፡ እንዲገታ ፡ እና ፡ እንዲከሽፍም ፡ ምልክዮሽ ፡ ከደነቀረበት ፡ ደንቃራዎች ፡ አንዱ ፡ ትርጒም-የለሹ ፡ "ብሔርተኝነት" ፡ ነበር ፤ ርሱንም ፡ ልባሙ ፡ ዐምሐራ ፡ እየነቀለ ፡ ያስወግደዋል ። ኢትዮጵያዊ ፡ ሀገራዊነት ፡ ይለምልም ፨

እግዚእናችንን ፡ የማስከበር ፥
*ሕግ ፡ መንግሥታችንን ፡ የመሥራት ፥*
*ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ የማቆም ፡*

ሀገራዊ ፡ ዐላማችንን ፡ ለመፈጸም ፥ በኢትዮጵያና ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የምንገኝ ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችን ፡ ለኾነው ፡ **ለኢ..ሀ.ሥ.አ. ፡ እናብር!**

የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።

ሥልጡንሕዝብና ።
www.slttunhzb.net

1 <u>ምልክዮሽ</u> ፤ "ኢምፔሪያሊዝም" ።


©ኢ..ሀ.ሥ.አ. ፥ 2018 ፡ ዓ.ም. ።